
| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "የበደል ፡ ውዝፍ ። " |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 2014 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2014-003 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

## ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

# የበደል ፡ ውዝፍ ።




እንኳን ፡ ለብርሃነ ፡ ትንሣኤው ፡ በሰላም ፡ አደረሳችኹ ! ወርኀ ፡ ሚያዝያ ፡ የትንሣኤ ፣ የሕይወት ፣ የትዳር ፣ የልምላሜ ፣ የድል ፣ የፍሥሓ ፡ ወር ፡ ነውና ፥ እንኳን ፡ ደስ ፡ አላችኹ ።

እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ያበለጸገውን ፡ ወር ፥ የሰው ፡ ልጅ ፥ ስግብግብነቱ ፡ በወለደው ፡ ብዙ ፡ በደሉ ፥ ከእነዚህ ፡ ጸጋዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ስላራቈተው ፥ እንሆ ፥ ወሩ ፡ የወገኖቻችንን ፡ መታረድ ፣ መፈናቀል ፣ መራብ ፣ መታረዝ ፡ የምንረዳበትን ፥ የገዳዮችን ፡ በነጻ ፡ መለቀቅና ፡ መንፈላሰስ ፡ የምንሰማበትን ፥ የዓለምንም ፡ ወደ ፡ ሦስተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ መንሸራተት ፡ የምናይበትን ፡ ክፉ ፡ ዘመን ፡ አስከተለብን ። የሰው ፡ ልጅ ፥ ተፈጥሮ ፡ ያዘጋጀለትን ፡ የፍሥሓ ፡ ዘመን ፡ ድንገት ፡ ዐጥቶ ፥ ወደጭንቅ ፡ እና ፡ ወደሐዘን ፡ ዘመን ፡ ተንከባለለ ። ከቶ ፡ መመለሻ ፡ ይኖረው ፡ ይኾን ፨ ቢኖረውስ ፥ የትኛው ፡ ይኾን ፨ ባይኖረውስ ፥ ጥፋቱ ፡ እምን ፡ ድረስና ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ይኾን ፨

መቼም ፥ ከኀሊና ፡ መታወር ፡ ይሰውር ! ነው ። ይህ ፡ ጥፋት ፡ እንደሚከተል ፡ ብዙ ፡ አንደበት ፡ ተናግሮ ፣ ብዙ ፡ ብርዕ ፡ ጽፎ ፡ ነበር ፤ ማን ፡ ሰምቶ ፡ ... ፥ ማንስ ፡ አስተውሎ ፡ ... ፨

***የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ሥምረትን ፡ (United Nations' Charter ን) ፡ በመጣስ*** ፥ ጥቂት ፡ ምዕራባውያን ፡ መንግሥታት ፡ ኢትዮጵያን ፡ የባሕር ፡ በር ፡ ለመንሣት ፥ ኤርትራ ፡ እንድትገነጠል ፡ ሲታገሉ ፦ *« ተዉ ፡ አይኾንም ! ኹለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ የተማረ ፡ በወልወል ፡ ግጭት ፡ መኾኑን ፡ አትዘንጉት »* ፡ ያሉ ፥ ኢ.ሀ.ሥ.አ.ን ፡ ጨምሮ ፥ ብዙ ፡ ድምፆች ፡ ነበሩ ፤ አልተሰሙም ። ምዕራባውያን ፡ ማስገንጠሉን ፡ ቀጠሉበት ። ይህም ፡ አልበቃቸው ፤ በ 1983 ፡ ዓ.ም. ፡ የደርግን ፡ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ ገርስሰው ፡ ሲጥሉ ፥ ደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ የተፋችውን ፡ የ"አፓርትሀይድ" ፡ ሥርዐት ፡ በበቀል ፡ መልክ ፡ በ 1987 ፡ ዓ.ም ፡ በ"ኢ.ፌ.ዴ.ሪ." ፡ ስም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ መልሰው ፡ ተከሉባት ። ኵሽ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ የለም ፤ ... ፡ አኹንም ፡ ቀጠሉበት ።

በገለልተኞች ፡ ሀገሮች ፡ ንቅናቄ ፡ በጐረበጠቻቸውና ፡ ጥርስ ፡ በነከሱባት ፡ ሀገር ፡ በዩጎስላቪያ ፡ የውስጥ ፡ ጉዳይ ፡ ምዕራባውያን ፡ ጣልቃ ፡ ገብተው ፥ አኹንም ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ሥምረትን ፡ በመጣስ ፥ በ 1988 ፡ ዓ.ም. ፡ ሀገሪቱን ፡ ፈጽመው ፡ አፈራርሰው ፡ ከዓለም ፡ ቢጋር ፡ ፋቋት ። ማንም ፡ ስላልተናገራቸው ፥ ቀጠሉበት ፤ በአፍጋኒስታን ፡ ሠለሱ ፣ በኢራቅ ፡ አረቱ ፣ በየመን ፡ ዐመሱ ፣ በዚምባብዌ ፡ ሰደሱ ፣ በቬኔዝዌላ ፡ ሰበቱ ... ። ዓለምን ፡ ከጦርነት ፡ ይጠብቃል ፡ ተብሎ ፡ የታመነበት ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ሥምረት ፡ ተደጋግሞ ፡ ተረመረመ ። ምዕራባውያን ፡ ኀይሎች ፦ *« ማንም ፡ ምንም ፡ አያመጣም ! »* ፡ ዐሉ ። ልጓም ፡ እንደወለቀላት ፡ በቅሎ ፡ ለጥቂት ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ልባቸው ፡ ፈነጩ ። በሄጌሊያኒዝም ፡ ጕሽ ፡ ጠላ ፡ የተሟሟቀ ፡ ዐፋሽ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2014 ፡ ዓ.ም. ።

አጐንባሽን ፣ ቀዳሽ ፡ አወዳሽን ፡ በፉኩያማ ፡ ሰውነት ፡ አብጅተውም ፥ ባንደበቱ ፦ « የአንግሎ-ሳክሰን ፡ ሥልጣኔ ፡ "ሊቤራል ፡ ዴሞክራሲ" ፡ የሥልጣኔን ፡ ዕንብር ፡ ነካ ፤ ታሪክ ፡ አበቃለት ! » ፡ አስሡኙ ።

ሐይ ፡ ባይ ፡ ታጥቶ ፡ ዓለም ፡ ግራ ፡ በተጋባበት ፡ ሰዓት ፥ የኮቪድ-19 ፡ ወረርሽኝ ፡ ባስደንጋጭ ፡ ኹኔታ ፡ ድንገት ፡ ተከሠተና ፥ ያበጠውን ፡ ኹሉ ፡ አስተንፍሶ ፥ ያስተካክለዋል ፡ ተብሎ ፡ ሲጠበቅ ፥ ርሱም ፡ በክትባት ፡ ተደለለ ፥ ... ፡ ለጊዜው ። ዘመን ፡ ዘመንን ፡ ወለደና ፦ « እኔም ፡ እንደ ፡ እናንተ ፡ በገዛ ፡ እጄ ፡ እካሳለኹ ! » ፡ ያሚል ፥ መስኮብ ፡ የተባለ ፡ ባለቀጠሮ ፡ ኀያል ፡ መንግሥት ፡ ተነሣ ፦ « በአንግሎ-ሳክሰኖች ፡ ዕባራ [1] ፡ የሚመራ ፡ **የሰሜን ፡ አትላንቲክ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ድርጅት ፡ (ሰ.አ.ቃ.ኪ..ድ.)** ፡ በኡክራይና ፡ በኩል ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ አጥቅቶኛል ፥ ዜጎቼንም ፡ ፈጅቶብኛልና ፥ ለመከላከል ፡ ወታደራዊ ፡ ገበራዬን ፡ ዝምሬያለኹ » ፡ ሲል ፥ ከተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ሥምረት ፡ ምሕቃፍ ፡ ውጪ ፥ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ መከላከሉን ፡ በይፋ ፡ አስታወቀ ። ጥንታውያን ፡ ግዛቶቼ ፡ ናቸው ፡ ያላቸውንም ፡ ክፍሎች ፡ ከኡክራይና ፡ ለመንጠቅ ፡ ዘመተ ። ... ፡ መስኮብስ ፡ ከማን ፡ አንሶ ፧

"ምን ፡ ቢነግሡ ፥ በገዛ ፡ እጅ ፡ አይካሱ" ፡ ነበር ፡ ተረቱ ። አንዱ ፡ ወገን ፡ ይህን ፡ ደንብ ፡ ደጋግሞ ፡ ሲጥሰው ፥ ሌላው ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፣ እጁን ፡ አጣምሮ ፡ ቢመለከት ፥ ኀያልነቱ ፡ ምኑ ፡ ላይ ፡ ነው ፧ ጊዜውን ፡ ጠብቆ ፥ በተመሳሳይ ፡ አካኼድ ፡ መራመዱ ፡ አይቀርምና ፤ መስኮብም ፡ ይህኑ ፡ ፈጸመ ። በመሪው ፡ በርእሰ ፡ ሀገር ፡ ቭላዲሚር ፡ ፑቲን ፡ አንደበት ፦ « የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ግንኙነት ፡ በአንግሎ-ሳክሰኖች ፡ ዕባራ ፡ የበላይነት ፥ ባንድ ፡ ዋልታ ፡ ሥር ፡ የተዋቀረበትን ፡ የዛሬውን ፡ አህጉራዊ ፡ ሥርዐት ፡ ለመቼውም ፡ ንደነዋል ! » ፡ ሲል ፥ እውነተኛውን ፡ የዘመቻውን ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፣ አንድያ ፡ ግቡን ፡ በግልጽ ፡ አስታውቋል ። "አንግሎ-ሳክሰን" ፡ የተባሉት ፡ መንግሥታት ፡ ተጠሪዎች ፡ ግን ፥ የአህጉራዊው ፡ ሥርዐት ፡ መናድን ፡ ቢያምኑም ፥ ችግሩን ፡ በሰላም ፡ ለመፍታት ፡ ሳይግደረደሩ ፥ ልጆቿ ፡ እንደተነኩባት ፡ ዐራስ ፡ ነብር ፡ የባሰውን ፡ የጦር ፡ መሣሪያን ፡ ለኡክራይና ፡ በማቀበል ፥ የእሳቱ ፡ አራጋቢዎች ፣ የችግሩ ፡ አባባሾች ፡ ኾኑ ። የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ በበኩላቸው ፦ « የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ሥምረት ፡ ተጣሰ ፣ ተረመረመ ! » ፡ ከማለት ፡ ሌላ ፥ መሠረታዊውን ፡ ችግር ፡ ሳይፈቱት ፥ አለባብሰውት ፡ ዐለፉ ። የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ሥምረት ፡ የተረመረመ ፡ ዛሬ ፡ አይደለም ፤ እጅግ ፡ የቈየ ፡ የበደል ፡ ውዝፍ ፡ አለ ።

ዛሬ ፥ አህጉራዊው ፡ ሥርዐት ፥ ምሥጥ ፡ እንደበላው ፡ ዕንጨት ፥ ድንገት ፡ እንክት ፡ ብሎ ፡ ተሰብሯል ፤ ከንግዲህ ፥ ለዓለም ፡ ሰላም ፡ ምንም ፡ ሌላ ፡ ዋስትና ፡ የለ ።

አኹንም ፡ ቢኾን ፥ ተገቢው ፡ ማስተካከያ ፡ በዓለም ፡ መንግሥታት ፡ በኅብረት ፡ ቢደረግ ፥ ገና ፡ ፈጽሞ ፡ አልመሸም ፤ የተሰበረውን ፡ መጠገን ፣ ሰላምንም ፡ መልሶ ፡ ማረጋገጥ ፡ ዛሬም ፡ ይቻላል ። ለዚህም ፡ ፈጣን ፣ ደፋርና ፡ ቍርጠኛ ፡ የጋራ ፡ ውሳኔ ፡ እና ፡ ክንዋኔ ፡ ያሻል ። በገቢር ፡ ይህ ፡ ይፈጸማል ፡ ለማለት ፡ ግን ፡ አንደፍርም ፤ እንዲያውም ፡ አይፈጸምም ፡ ማለቱ ፡ ይቀላል ። አንድ ፡ አፍታ ፡ ተስፈኛዎች ፡ እንኹንና ፥ የ"ይቻላል"ን ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ እንዲህ ፡ እንደርድረው ፦

1ኛ ፤ ቢያንስ ፥ ባለፉት ፡ 30 ፡ ዓመታት ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታትን ፡ ሥምረት ፡ በገፍ ፡ የጣሱት ፡ ኀይሎች ፡ ኹሉ ፡ ጥፋቶቻቸውን ፡ በይፋ ፡ ይመኑ ፥ የተበደሉትንም ፡ በይፋ ፡ ይቅርታን ፡ ይጠይቁ ፤

2ኛ ፤ የተባበሩት ፡ መንግሥታትን ፡ ሥምረት ፡ በመጣስ ፡ ግፍ ፡ የተፈጸመባቸው ፡ ሀገሮች ፡ ኹሉ ፥ ጕዳያቸው ፡ በአህጉራዊ ፡ የፍርድ ፡ ችሎት ፡ ታይቶ ፥ ፍትሓዊ ፡ ውሳኔን ፡ ያግኙ ፤ ለደረሰባቸው ፡ ጕዳትና ፡ ክሳራም ፡ ተገቢውን ፡ ካሳ ፡ ያግኙ ፤ የተባበሩት ፡ መንግሥታትን ፡ ሥምረት ፡ በመጣስ ፡ በሀገሮችና ፡ በሕዝቦች ፡ ላይ ፡ ዕልቂትን ፡ ያደረሱ ፡ መንግሥታትና ፡ በኀላፊነት ፡ የነበሩና ፡ ያሉ ፡ መሪዎቻቸውም ፥ ጕዳያቸው ፡ በአህጉራዊ ፡ መርማሪ ፡ ድርገት ፡ ታይቶ ፥ አጥፊነታቸው ፡ ሲረጋገጥ ፥ በአህጉራዊ ፡ የፍርድ ፡ ችሎት ፡ ይዳኙ ፤

3ኛ ፤ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፥ በ1938 ፡ ዓ.ም. ፡ ሲቋቋም ፡ በዓለም ፡ የነበረው ፡ መንፈስና ፡ ኹኔታ ፡ ዛሬ ፡ ስለ ፡ ተለወጠ ፥ ሥምረቱም ፡ ይህኑ ፡ እንዲያገናዝብ ፥ በተለይ ፡ በጸጥታ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አወቃቀር ፡ ረገድ ፥ ተፈላጊው ፡ ማዘመኛ ፡ ኹሉ ፡ ይደረግለት ።

እላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ማስተካከያዎች ፡ ቢደረጉ ፥ ከንግዲህ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ጥሰቶችን ፡ ኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ለማገድና ፡ የዓለምን ፡ ሰላም ፡ ለመጠበቅ ፣ ለማረጋገጥም ፡ በረዳ ፡ ነበር ።

ዳሩ ፡ ግን ፥ ነገሩ ፡ የሕልም ፡ እንጀራ ፡ ነው ። ከ"ኮንኪስታዶሮች" ፡ ምዝበራና ፡ የባሪያ ፡ ንግድ ፡

---

1 አንግሎ-ሳክሰን ፡ ዕባራ ፤ Anglo-Saxon coalition ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2014 ፡ ዓ.ም. ።

እስከ ፡ "ኮሎኒያሊስቶች" ፡ ፍጅትና ፡ ብዝበዛ ፥ ለ 600 ፡ ዓመታት ፡ በንስሓ ፡ እና ፡ በይቅርታ ፡ ያልነጹት ፥ ወይ ፡ በቅጣትና ፡ በካሳ ፡ መዝገቦቻቸው ፡ ያልተዘጉት ፡ የዓለም ፡ በደሎች ፡ ከመድለባቸው ፡ የተነሣ ፥ ኀያላኑ ፡ ቀና ፡ ሐሳብን ፡ የሚሰሙበትን ፡ እዝነ ፡ ልቡና ፣ ቀና ፡ መንገድን ፡ የሚያዩበትን ፡ ዐይነ ፡ ልቡና ፡ ስላጡ ፥ ኹሉም ፡ በእየወገኑ ፥ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ ፈጽሞ ፡ የሚያጠፋበትን ፡ ጊጣንና ፡ ተንኰል ፣ መርዝና ፡ መሣሪያ ፡ ያራቅቃል ፡ እንጂ ፥ የምን ፡ መለሳለስ ፡ ነው ፡ ... ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሰላምን ፡ የማውረዱ ፡ ተስፋ ፡ ለመቼውም ፡ የተቀጨ ፡ ይመስላል ። ታዲያ ፥ ሰላማዊውን ፡ መፍትሔ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ቢገፋው ፥ የእግዚአብሔር ፡ ፍትሕ ፡ በማይመረመር ፡ መንገዱ ፡ ከመፈጸም ፡ የሚከለክለው ፡ አይኖርምና ፥ መዐቱ ፡ ሊወርድብን ፡ ግዴታ ፡ ኾኗል ።

ወደ ፡ ውድ ፡ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጓሊናችንን ፡ መለስ ፡ ስናደርገው ፥ የዕለት ፡ ጕርሡን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ የሕይወት ፡ ዋስትናውንም ፡ ያጣው ፡ የመከረኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ኹኔታ ፡ በተለይ ፡ ያሳስበናል ፤ የርሱ ፡ መከራ ፡ ጊዜ ፡ አይሰጥምና ። በሬ ፡ 200'000 ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ገባ ፡ ብለን ፡ እንዳንቈጭ ፥ ድኻው ፡ መቼ ፡ በሬ ፡ በልቶ ፡ ያውቃል ፧ ይልቅስ ፡ አንድ ፡ እንቍላል ፡ 20 ፡ ብር ፡ ገባ ፡ የሚለው ፡ የባሰ ፡ ያሳስባል ። የዋጋ ፡ ንረት ፡ ከቍጥጥር ፡ ውጭ ፡ ኾኗል ። ድኻው ፡ ምን ፡ በልቶ ፡ ይደር ፧ የሰው ፡ ልጅ ፡ በገዛ ፡ ሀገሩ ፡ ዐርሶ ፣ ነግዶ ፡ እንዳይበላ ፡ በሀገራዊነቱ / በዐምሐራነቱ ፡ ምክንያት ፡ የሚፈናቀልና ፡ የሚገደል ፡ ከኾነ ፥ እሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ በውንብድና ፡ የወጣውን ፡ ራሱን ፡ አፈናቃዩን ፡ ለምን ፡ አናፈናቅለውም ፧ እስከ ፡ መቼ ፡ እዬዬ ፡ እና ፡ ልቅሶ ፧ ዓለም ፡ በቋፍ ፡ በምትገኝበት ፡ ሰዓት ፡ ለምኑ ፡ ነው ፡ የምንሣሣው ፧

ልጆች ፡ ኾነን ፥ ታላላቆቻችን ፡– « የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ጐመን ፡ መብላት ፡ አቅቶት ፥ ዘላለሙን ፡ ጐመን ፡ ሲበላ ፡ ይኖራል » ፡ ሲሉ ፡ እንሰማ ፡ ነበር ። ዛሬም ፡– « የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ትዕግሥትን ፡ አበዛ » ፡ ተብሎ ፥ የማያስነቅፈው ፡ ጠባዩ ፡ ሲያስነቅፈው ፡ እንሰማለን ። እውነት ፡ ነው ፥ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ትዕግሥት ፡ ማለቂያ ፡ የሌለው ፡ ይመስላል ። ነገር ፡ ግን ፡ « ትዕግሥተኛ ፡ ሰው ፡ ከኀያል ፡ ሰው ፡ ይሻላል » ፡ እንዳለው ፡ ጠቢቡ ፡ ሰሎሞን ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ሕያው ፡ ታሪክ ፡ ያስታወስን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ « ተሸነፈ ፡ ... » ፣ « ሞተ ፡ ... » ፣ « ተቀበረ ፡ ... » ፡ በተባለበት ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፥ ያልታሰበ ፣ ያልተጠበቀ ፡ መዐት ፡ ወርዶ ፥ የመቃብሩን ፡ ድንጋይ ፡ ፈንቅሎለት ፥ በዠግኖቹ ፡ መሥዋዕት ፡ ባሸናፊነት ፡ ተነሥቶ ፡ በዓለም ፡ አደባባይ ፡ ተመልሶ ፡ ብቅ ፡ ይላል ። በኹለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ዋዜማ ፡ እና ፡ ማግስት ፡ የታየውን ፡ ማስታወስ ፡ ልብን ፡ ያሞቃል ። በእነዚህ ፡ የጨለማ ፡ ዘመኖች ፡ ኹሉ ፥ የኢትዮጵያ ፡ የቍርጥ ፡ ቀን ፡ ልጆች ፡ ተነሥተው ፥ ጊዜው ፡ የጠየቀውን ፡ መራራ ፡ ትግልና ፡ መሥዋዕትነት ፡ በዠግንነት ፡ በመክፈል ፡ ያሳዩት ፡ የሀገር ፡ ቤዛነት ፡ ለዘላለም ፡ ይታወሳል ።

እንሆ ፡ ዛሬም ፥ ኢትዮጵያን ፡ ባስጨነቁ ፡ ኀያላን ፡ መንግሥታት ፡ ላይ ፡ ሌሎች ፡ ኀያላን ፡ ተነሥተውባቸዋል ። በመንደር ፡ ገነኖችና ፡ በጥፋት ፡ ቡድኖች ፡ መሣሪያነት ፡ ከሩቅ ፡ የሚመሯው ፡ ኢትዮጵያን ፡ የመበታተንና ፡ የማጥፋት ፡ ፀረ-ሀገራዊ / ፀረ-ዐምሐራ ፡ ደባ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ተጋልጧል ። የደባው ፡ ዘዋሪዎች ፡ የባሰ ፡ ጠር ፡ ድንገት ፡ ወድቆባቸው ፡ የሞት ፡ ሽረት ፡ ትግል ፡ ስለ ፡ ገጠሙ ፥ ኀይላቸው ፡ ተከፍሏል ፥ የድቅናቸው ፡ ቀደም ፡ ተከተል ፡ ተዘበራርቋል ፤ ጦርነቱም ፡ ዐያሌ ፡ ስያሳውያንና ፡ ጥርየታውያን ፡ መናጋቶችን ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ስለሚያስከትል ፥ የኢትዮጵያ ፡ ባለጋራዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የዘረጓቸውን ፡ እጆቻቸውን ፡ ፈጽመው ፡ ሊሰበስቡ ፡ ይገደዳሉ ።

በኢትዮጵያ ፡ ወገን ፥ የቍርጥ ፡ ቀን ፡ ልጆቿ ፡ ሊታደጓት ፡ በእየአግጣጫው ፡ ተነሥተዋል ። ዜናቸውን ፡ ማንም ፡ የማያሰማላቸው ፡ እልፍ ፡ አእላፍ ፡ ዐርበኞች ፡ ተፈጥረዋል ፤ ሕዝብም ፡ ዐቅፏቸዋል ።

ኢትዮጵያ ፡ ሆይ ! የመከራሽ ፡ መጨረሻ ፡ ተቃርቧል ፨

እግዚአናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡
ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!
ኢ ሀ ሥ አ
የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።
ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net